# 6ኛ ዙር አንደኛ የስራ ዘመን በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፕላን ፣በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢፌዴሪ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የ2014 ዓ.ም የአንደኛ ሩብ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተሰጠ ግብረ-መልስ

ታህሳስ /2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# 1. መግቢያ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን ተልዕኮ ህግ የማውጣት፣አስፈጻሚ አካላትን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ እና የውክልና ተግባራትን እንዲያከናውኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 55 ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።ምክር ቤቱም የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት በም/ቤቱ የአሰራርና የአባላት ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008/እንደተሻሻለው የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 3/2014 መሰረት አስራ አንድ ቋሚ ኮሚቴዎችን ሲያደራጅ የፕላን፣በጀትና ፋይናንስ ጉ/ቋ/ኮሚቴ አንዱ ነው።ቋሚ ኮሚቴው ከሚያከናውናቸዉ ተግባራትም በህገ-መንግስቱ መሠረት የፌዴራል ስርዓቱን የተከተለ የክትትልና ቁጥጥር እንዲያካሂድ ተግባር እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

በመሆኑም የኢፌድሪ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የአንደኛ ሩብ ዓመት የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅተው ልከዋል።በዚህሁ መሰረት የፕላን፣በጀትና ፋይናንስ ጉ/ቋ/ኮሚቴያችን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ሰነድ በመገምገም ጥንካሬዎችና እጥረቶችን በመለየት እንዲሁም የትኩረት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ከዚህ እንደሚከተለው ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡

# 2. በጥንካሬ የተለዩ ጉዳዮች

- ሀገራዊ የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ ዝግጅት የልማት ዕቅድ ፅንሰ ሃሳብ መዘጋጀቱ ፡፡
- የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚዉ ላይ እያደረሰ ያለዉን ጫና ለመቆጣጠር ፕሮግራም ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ ለዋጋ ንረት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ላይ ትንታኔ የሚያደርጉና የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያስቀምጡ ጥናቶችን እንዲያካሄዱ የተቀመጠው አቅጣጫ፡፡
- ሚኒስትር መ/ቤቱ የዘርፈ ብዙ የድህነት አመልካች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል የመነሻ የጥናት ሰነድ ለመዘጋጀት የዘርፈ ብዙ ድህነትን ለመለካትና ለመተንተን የቤተሰብ ገቢና ወጪ የናሙና ጥናት እና የኑሮ ደህንነት የናሙና ጥናት መረጃዎችን በመሰብሰብ ላይ መሆኑና ኢ-እኩልነት በረዥም ጊዜ ሁኔታ ለድህነት መባባስ ምክንያት ሊሆን የሚችልባቸውንና የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማጥናት የጥናቱ መነሻ ሀሳብ መዘጋጀቱ፡፡

- በፌዴራል ተቋም ደረጃ የዲጂታል ክትትልና ግምገማ ሲስተም ተግባራዊ በመደረጉ የተቋማቱ እቅድ ከ 2,700 በላይ ቁልፍ መለኪያዎች ወደ ሲስተሙ ኢንኮድ መደረጉ እንዲሁም ተቋማት ሪፖርታቸውን በሲስተሙ እንዲልኩ ቴክኒካል ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸሙ ከፍተኛ መሆኑ ፡፡
- የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ማንዋሎች እና ቅፆችን የማሻሻል እና የፕሮጀክት ፅነሰ ሀሳብ፣የአዋጭነት ጥናት እና የትግበራ ዕቅድ መመሪያዎች ያለባቸውን ክፍተት ለመሙላት መመሪያዎቹ እንዲሻሻሉ መደረጉ፡፡
- ሚኒስትር መ/ቤቱ የተጠሪ ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም በሪፖርቱ አካቶ ስለመላኩ

### 3. በእጥረት የተለዩ ጉዳዮች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የመደበኛው በጀት አጠቃቀም ንፅፅር የአረቱ ፕሮግራሞች አማካይ አፈጻጸም 45.3% ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ለአዲስ ቅጥር ሰራተኞች የቅድመ ሥራ ማስተዋወቂያ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ስልጠና አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የመ/ቤቱን ድረ-ገፅ ማስተዳደር የመ/ቤቱ ድረ-ገፅ የማልማት ስራ ቢጠናቀቅም ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት አለማስጀመር።

## 4. ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች

- የህፃናት ማቆያ ግንባታን ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን በመከታተል የግንባታ ስራውን ማስመጀመርና ወደ ተግባር መቀየር፡
- በታቀደው መሰረት የ3 ዓመት (2414-2016 በጀት ዓመት) የዕቅድ ሰነድ በተዘጋጀው የማክሮ ፍሬም ወርክ ሰነድ መሰረት አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ አጠቃላይ የልማት ዕቅድ ክለሳ ማድረግ ፣
- ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚዉ ላይ እያደረሰ ያለዉን ጫና ለመቆጣጠር የሚያስችል ፕሮግራም ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ለዋጋ ንረት ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች ላይ ትንታኔ የሚያደርጉና የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያስቀምጡ ጥናቶችን እንዲያካሄዱ ለሚመለከታዉ አካል በተቀመጠው አቅጣጫ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ስራውን የማስተባበር ሃላፊነቱ በትጋት መወጣት ይኖርበታል፡፡
- የተዘጋጀው የፕሮጀክቶች የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሠነድ አፈፃፀሙን በመከታተል የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ከቅድመ-ትግበራ ስርዓት ፣ ከፕሮጀክቶች ክትትል ስርዓት፣ ከዴስክ ሪቪውና ከመስክ ክትትል አንፃር፣ከፕሮጀክቶች ግምገማ ስርዓት ከቅድመ-ትግበራ፣ከአጋማሽ ዘመን ግምገማ፣ከመጨረሻ ዘመን ግምገማ እና ከፕሮጀክቶች ስኬትና ፋይዳ ግምገማ፣ተሞክሮዎችን ከመቀመርና ተደራሽ ከማድረግ እንዲሁም ከቅንጅታዊ አሰራር፣ከአቅም ግንባታ እና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንፃር በመከታተልና በመገምገም አፈፃፀማቸውን ማሻሻልና በተዘጋጀው የክትትልና ሪፖርት ሥርዓትን ለመተግበር የለማውን ሶፍትዌር አሰራሩን በቅርብ በመከታተል እንዲሻሻል ማድረግ ይጠበቃል።

## 5. ማጠቃለያ

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነቶች ኢኮኖሚውን በረጅምና በመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ በመምራት ፈጣን ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲሁም ዘላቂና ፍትሀዊ ልማት እንዲረጋገጥ ማስቻል ሲሆን የአንደኛ ሩብ ዓመት የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ በላከው መሠረት የፕላን፣በጀትና ፋይናንስ ጉ/ቋ/ኮሚቴያችን የአፈጻጸም ሪፖርቱን በመገምገም አቅጣጫ አስቀምጠዋል።

በዚህሁ መሰረት የአፈጻጸም ሪፖርቱን ሰነድ በመገምገም በጥንካሬ፣በእጥረት እና ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ያለውን በመለየት ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ግብረ መልስ ተሰጥቷል።